**የኮርስ መጨረሻ (EOC) ምዘናዎች/ግምገማዎች**
**ስለ መንግስት እና ሳይንስ**
***በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች***

**የሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም** (MCAP)በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ይዘት ላይ የተማሪ እድገትን በተመለከተ ለመምህራን፣ ለወላጆች እና ለማህበረሰብ መረጃ ይሰጣል። ጠንካራ የምዘና ስርዓት በመዘርጋት፣ ባለድርሻ አካላት ትምህርት ቤቶች እንዴት እየሰሩ እንደሆኑ እና የተማሪን እድገትና ስኬት ለመደገፍ የቱ ጋ እርዳታ መደረግ እንዳለበት ያስገነዝባል። የመመረቂያ መስፈርቶች የኮርስ ክሬዲቶችን፣ MCAP ምዘናዎችን እና የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶችን ያካትታሉ። ስለ ተማሪዎች እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ የመመረቂያ መስፈርቶችን በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ያገኛሉ፡- https://www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/graduation-requirements

ከ 2023-2024 የትምህርት አመት ጀምሮ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች (የመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል (FTNG) 2024፣ 2027 የሚመረቁ)፣ ስለ መንግስት እና የሳይንስ ትምህርት የሜሪላንድ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስነመንግስት እና የሳይንስ ኮርሶች የመጨረሻ ክፍል የተማሪዎች ምዘና 20 በመቶ (ፐርሰንት) ይያዝላቸዋል። ኮርሱ የተወሰደው በትምህርት አመቱ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ ከሆነ ይህ 20 በመቶው (ፐርሰንት) ወደ ሴሚስተር B የመጨረሻ ውጤት ላይ ይሰላል። ተማሪዎች ለመመረቅ EOC ፈተናዎችን ማለፍ አይጠበቅባቸውም፣ ነገር ግን የኮርስ ክሬዲት ለማግኘት ኮርሱን ማለፍ አለባቸው። አንድ ተማሪ EOC ፈተና ላይ ቢያንስ ዝቅተኛውን 50% ውጤት ማግኘት ያለበ(ባ)ት።

ከዚህ በታች የተመለከተው MCAP መንግስት እና LS MISA ፈተና በተማሪዎች የዘጠነኛ ክፍል ውጤት ላይ በመመስረት የመጨረሻ ውጤት ላይ 20% እንደሚሰላ የሚያመለክት መሸጋገሪያ ነው።

| | 9ኛ ክፍሎች FTNG 2024 | 10ኛ ክፍሎች FTNG 2025 | 11ኛ ክፍሎች FTNG 2026 | 12ኛ ክፍሎች FTNG 2027 |
|---|---|---|---|---|
| **የትምህርት ዓመት (SY) 2023-2024** | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ |
| **የትምህርት ዓመት (SY) 2024-2025** | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ |
| **የትምህርት ዓመት (SY) 2025-2026** | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = መሳተፍ ብቻ |
| **የትምህርት ዓመት (SY) 2026-2027** | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት |

MCAP ስለ መንግስት እና LS MISA EOC ፈተናዎችን የሚመለከቱ የኮርስ ኮዶች እና የኮርሶቹ ርዕሶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች MCAP ምዘና EOC ፈተና የሚሰጥባቸው ኮርሶች እነዚህ ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ኮርሶች በጊዜ መርሐግብር ካርዳቸው ላይ በኮርሱ መለያ መጨረሻ ላይ 'x' ተጽፎበት ያገኙታል።

| ስነመንግስትን ኮርሶች | | LS MISA ኮርሶች | |
|---|---|---|---|
| **የኮርስ መለያ** | **የኮርሱ ርእስ** | **የኮርስ መለያ** | **የኮርሱ ርእስ** |
| **SOC2003B** | ብሔራዊ የስቴት እና የአካባቢ (NSL) ስነመንግሥት B | **SCI2000B** | ባዮሎጂ B |
| **SOC2004B** | የላቀ (ኦነርስ) ብሔራዊ የስቴት እና የአካባቢ መንግስት B | **SCI2001B** | የላቀ (ኦነርስ) ባዮሎጂ B |
| **SOC2025B** | MCPS PIB ስነመንግስት B | **SCI2013B** | የላቀ ደረጃ (አድቫንስድ) ሳይንስ 4 ባዮሎጂ B |
| **SOC2083B** | RMS ስነመንግስት B | **SCI2049B** | የከባቢ ሳይንስ ባዮሎጂ B |
| | | **SCI2084B** | MCPS PIB ባዮሎጂ B |
| | | **SCI2103B** | RMS ባዮሎጂ 1B |
| | | **SCI2108** | የላቀ (ኦነርስ) ባዮሎጂ ጣምራ ክፍለጊዜ |

**<u>በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች</u>፡-**

**አጠቃላይ**

Q: **አሁን ባለው MCAP EOC ፈተና እና ባለፈው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዘና (HSA) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

A: HSA ምዘና መርሃ ግብር ተማሪ የመመረቂያ ምዘና ለማሟላት የማለፊያ ነጥብ የሚያገኙበት ተከታታይ የሁለተኛ ደረጃ ምዘና ነበር። ተማሪ በምዘናው ላይ ያሳየ(ች)ው አፈጻጸም በተማሪው(ዋ) የመጨረሻ ውጤት፣ በኮርሱ ላይ ወይም ተዛማጅ የኮርስ ክሬዲቶችን በማግኘት ላይ ምንም ተጽእኖ አልነበረውም።

MCAP EOC ፈተና በተማሪ የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ላይ ይካተታል። የተማሪ EOC ፈተና ማለፍ የተለየ የመመረቂያ መስፈርት ተደርጎ አይቆጠርም።

**ያሉት መገልገያዎች/አኮሞዴሽንስ**

Q: **EOC በልዩ ሁኔታ የተሰናዱ ፈተናዎች አሉ?**

A: አዎ፣ EOC ፈተናዎች በብሬይል፣ በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ እና በትልልቅ ጉልህ ፊደላት ህትመት ይገኛሉ። እንደ ሁልጊዜው፣በተማሪ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም፣ 504 እቅድ፣ እና/ወይም የእንግሊዘኛ ተማሪ እቅድ መሠረት የፈተና መገልገያዎች/አኮሞዴሽንስ ይኖራሉ።

ከፍተኛ የግንዛቤ (ኮግኒቲቭ) እክል ያለባቸው ተማሪዎች ሌላ አማራጭ ምዘናዎችን ለመውሰድ መመዝገብ ይችላሉ። አማራጭ ምዘናዎችን እንደአግባቡ ለመውሰድ ካልተመዘገቡ በስተቀር IEP እና 504s ያላቸው ተማሪዎች የተሰናዳውን EOC ፈተና መውሰድ አለባቸው። ተለዋጭ ምዘናዎችን የሚወስዱ ተማሪዎች በኮርሱ የመጨረሻ ውጤታቸው 20% በመቶ የምዘና ውጤት እንዲኖራቸው ግዴታ አይሆንም።

**Q: EOC ፈተናዎች ከእንግሊዝኛ በስተቀር በሌሎች ቋንቋዎች ይሰጣሉ?**

A: 2023-2024 የትምህርት አመት እና ከዚያም በኋላ፣ EOC ፈተናዎች ለተማሪዎች የስፓንሽኛ ትርጉም እትም ይኖራል።

**Q: EOC ፈተና በስፓንሽኛ ትርጉም ለመውሰድ ብቁ ሚሆነው ማነው?**

A: 2023-2024 የትምህርት አመት በአሁኑ ጊዜ LEP አኮሞዴሽን 7g. ያላቸው ተማሪዎች በስፓንሽኛ ትርጉም ለመውሰድ ብቁ ናቸው። ከጁላይ 1, 2024 ጀምሮ ይህ ኮድ 1w ይሆናል። በስፓንሽኛ የተዘጋጀ በኮምፒውተር የሚሰጥ ምዘና።

**የኮርስ ማጠናቀቂያ (EOC) ውጤት በተማሪ ውጤቶች ላይ ያለው ነፀብራቅ**

**Q: በሴሚስተር ውጤት ላይ EOC ውጤት ምን አይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል?**

A: በተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ የስነመንግስት እና የሳይንስ ኮርሶች የመጨረሻ ውጤት ላይ EOC ውጤት 20 በመቶ (ፐርሰንት) ይሰላል። "B" ኮርስ በትምህርት አመቱ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ ቢወሰድም ሴሚስተር B የመጨረሻ ውጤት ላይ ይህ 20 በመቶ (ፐርሰንት) ይሰላል። የሴሚስተር "B" አጠቃላይ ውጤት ለእነዚህ ተደጋጋፊ ኮርሶች 3ኛ የማርክ መስጫ ጊዜ ውጤት (40%)፣ 4ኛ የማርክ መስጫ ጊዜ ውጤት (40%) እና MCAP የኮርስ ማጠቃለያ (EOC) የፈተና ውጤት (20%) ይሆናል። MCPS የውጤት (ማርክ) አሰጣጥ ሰንጠረዥ የተማሪን የሁለተኛ ሴሚስተር መጨረሻ B ሴሚስተር ወይም ሴሚስተር "B" ውጤት በእያንዳንዱ ሩብ ክፍለጊዜ የሚፈለገውን የትምህርት አፈጻጸም ደረጃ እና የኮርስ መጨረሻ ምዘና ውጤት ያሳያል።

**Q: የስነመንግስት እና LS MISA EOC ውጤቶች የሚገኙት መቼ ነው?**

A: መምህራን ጁን 10 በሚውልበት ሣምንት ውስጥ ውጤቱ ይደርሳቸዋል፣ ነገር ግን StudentVue ላይ ወይም በአስተማሪ የውጤት መስጫ መጽሔት ላይ አይለጠፉም። መምህራኖቻቸው ለተማሪዎች ውጤታቸውን ሲገልጹላቸው፣በሪፖርት ካርዳቸው እና 2024 መገባደጃ ላይ ወደ ቤት በሚላኩት የተማሪ ግላዊ የትምህርት አፈጻፀም ሪፖርት (ISR) ላይ የፈተና ውጤት ማየት ይችላሉ።

**Q: አንድ ተማሪ የሚጠበቅበ(ባ)ትን EOC ካጠናቀቀ(ች) እና EOC ፈተና ካለፈ(ች) ቀጥሎ ምን ይደረጋል?**

A: የማጠናቀቂያ ኮርሳቸውን 20% በመቶ የሚሆነውን EOC ፈተና ወስደው ኮርሱን ያለፉ ተማሪዎች የመመረቂያ ምዘና መስፈርቱን አሟልተዋል ማለት ነው።

**Q: አንድ ተማሪ EOC ፈተና ቢወድቅ/ብትወድቅ ነገር ግን ኮርሱን ካለፈ(ች) ምን ይሆናል?**

A: EOC ፈተና ለተማሪው(ዋ) የመጨረሻ ኮርስ ውጤት 20% በመቶውን ይይዛል። የመመረቂያ መስፈርትን ለማሟላት EOC ምዘና የማለፍ መስፈርት የለም። ተማሪ የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ላይ ካለፈ(ች) የኮርሱን እና የመመረቂያ መስፈርቶችን ያሟላል/ታሟላለች።

**Q: ተማሪ ኮርሱን እና EOC ፈተና ቢወድቅ ምን ይሆናል?**

A: የሴሚስተር B ኮርስ የወደቁ እና EOC ፈተና የወደቁ ተማሪዎች የሴሚስተር B ኮርስ እንደገና መውሰድ እና EOC እንደ የመጨረሻ ውጤት 20% በመቶ መውሰድ አለባቸው። ከዚህ በታች

ያለውን EOC ማካካሻ እና ኮርስ በድጋሚ መውሰድ በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ይመልከቱ። አማራጭ የኮርስ ክሬዲት ለማግኘት ተማሪዎች LEA የክሬዲት ማሚያ ኮርስ መውሰድ ይችላሉ። የክሬዲት ማሚያ ኮርሶች EOC እንደ መጨረሻ ውጤት 20% በመቶ ማካተት አያስፈልጋቸውም። ተማሪዎች ለክሬዲት ማሚያ ብቁ መሆን አለመሆናቸውን በተመለከተ የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ማነጋገር አለባቸው።

Q: **EOC ነጥብ እንዴት ወደ ፊደል ውጤት ይቀየራል?**

A: **ለመጨረሻው የኮርስ ምዘና የነጥብ ውጤት ለውጥ** (GCS) **ሞዴል** ዓላማው በምዘናው ላይ የተማሪን ውጤት ወደ ፊደል ውጤት ሚዛን መለወጥ ነው። **GCS ሞዴል ላይ EOC ፈተና ዝቅተኛው የውጤት ነጥብ 50%** ነው። GCS ሞዴል ተማሪዎች EOC ፈተና ላይ ጥሩ ውጤት በማምጣት የመጨረሻውን ኮርስ እንዲቀጥሉ ወይም እንዲጨምሩ ያስችላቸዋል፤ እንዲሁም ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ጠንከር ያለ ፈተና ይሰጣቸዋል።

**የውጤት ነጥብ ማመሳከሪያ (GCS) ሰንጠረዥ**

| በፊደል የሚሰጥ ውጤት | GCS ውጤት | LS MISA<br>የውጤት ነጥብ ሚዛን | የአሜሪካ ስነመንግስት<br>የውጤት ነጥብ ሚዛን |
|---|---|---|---|
| A | 90-100 | 757-850 | 466-650 |
| B | 80-89 | 744-756 | 442-465 |
| C | 70-79 | 737-743 | 419-441 |
| D | 60-69 | 731-736 | 394-418 |
| E | 50-59 | 650-730 | 240-393 |

**የነጥብ ውጤት መለወጫ ሠንጠረዥ ምን ማለት ነው?**

- "የፈተና ነጥብ ሚዛን" የተማሪን EOC አጠቃላይ ፈተና (LS MISA ወይም የአሜሪካ ስነመንግስት) ይመለከታል። ፈተናው ላይ በትክክል የተመለሱ ጥያቄዎች ላይ የተመሰረተ ነው።
- "GCS ነጥብ" የሚያመለክተው በፈተና ነጥብ ሚዛን ላይ የተመሰረተውን የውጤት ነጥብ ልኬት ነው። ዝቅተኛው 50 እና ጣሪያው 100 ነው።
- "በፊደል የሚገለጽ ውጤት" የሚያመለክተው A እስከ E ተማሪ EOC ፈተና ላይ ያገኘ(ች)ውን ውጤት ሲሆን ይህም የመጨረሻ ኮርስ ውጤት 20% በመቶውን ይይዛል። በፊደል የሚሰጥ ውጤት GCS የነጥብ አሰጣጥ ላይ የተመሰረተ ነው፡ GCS ነጥብ 90 እና ከዚያ በላይ ከሆነ "A" ፊደል 80 እስከ 89 ከሆነ "B" 70 እስከ 79 ከሆነ "C" 60 እስከ 69 ከሆነ "D" እና 59 እና ከዚያ በታች "E" የፊደል ውጤት ይጻፋል።

EOC ማካካሻ እና በድጋሚ ኮርስ መውሰድ

**Q: ተማሪ በፈተና መስጫ ወቅት EOC ፈተና ካመለጠው/ካመለጣት ምን ይሆናል?**

A: COMAR የመመረቂያ መስፈርቶች መሰረት ተማሪው(ዋ) ዲፕሎማ ለማግኘት የትምህርት ምዘናውን መውሰድ ይኖርበ(ባ)ታል። 2023-2024 የትምህርት አመት፣ ተማሪ በምክንያት ወይም ያለምክንያት ከቀረ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) የሴሚስተሩን ኮርስ አላሟላ(ች)ም ተብሎ ይመዘገባል። MCAP ፈተና ከወሰዱ በኋላ፣ የመጨረሻው የኮርስ ውጤት በዚያን ጊዜ ከተወሰደው ፈተና የተገኘውን ውጤት በመጠቀም ይሰላል። EOC ፈተና ያልወሰዱ ተማሪዎች በሠመር ወቅት ከጁላይ 22 እስከ 26 የሚሰጥ EOC ፈተና እንዲወስዱ ይበረታታሉ። ለሠመር EOC ፈተና ለመመዝገብ ወይም ሌሎች አማራጮችን ለመነጋገር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤትዎን ካውንስሊንግ ቢሮ ያነጋግሩ።

**Q: በሠመር የፈተና መስጫ ወቅት EOC የሚወስዱ ተማሪዎች አዲስ የሪፖርት ካርድ ያገኛሉ?**

A: አዎ፣ ያላሟሉ ተማሪዎች በስፕሪንግ የፈተና መስጫ ወቅት ፈተና ባለመውሰዳቸው ወይም ምዘናውን የወሰዱት ከሜይ 15 በኋላ በመሆኑ ምክንያት EOC ውጤታቸው ከደረሰ በኋላ የሰሚስተር ውጤታቸው ተሰልቶ ሁለተኛ የሪፖርት ካርድ ያገኛሉ። ከሜይ 15 በኋላ የተሰጡ የፈተና ውጤቶች ካርዶች ወደ ህትመት ከመግባታቸው በፊት ስላልደረሱ የመጀመሪያ የሪፖርት ካርዳቸው ላይ አልተሟላም የሚል ይንፀባረቃል።

**Q: ተማሪዎች የኮርስ ውጤታቸውን ለማሻሻል EOC እንደገና እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል?**

A: አይፈቀድም፤ ተማሪዎች ከፍ ያለ ነጥብ ለማግኘት EOC ኮርስ ዳግመኛ ከመውሰዱት የተለየ ሊሆን አይችልም።

**Q: ተማሪዎች የኮርስ ውጤታቸውን ለማሻሻል የሴሚስተር B ኮርስ እንደገና እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል?**

A: ተማሪዎች የኮርስ ውጤታቸውን ለማሻሻል የሴሚስተር B ኮርስ እንደገና መውሰድ ይችላሉ፣ እና ኮርሱን እንደገና ከወሰዱ EOC እንደገና መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

**Q: በሠመር ትምህርት ወቅት ተማሪዎች የሴሚስተር B ኮርስ እንደገና የመውሰድ እድል ይኖራቸዋል?**

A: ለመጀመሪያ ጊዜ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ባዮሎጂ እና NSL በሠመር ትምህርት ክፍለጊዜ 1 የሴሚስተር B ኮርሶች ይሰጣሉ። ተማሪዎች ከጁላይ 22 እስከ 26 ባለው የሠመር የፈተና መስጫ ወቅት EOC ፈተና ከመውሰዳቸው በፊት በክፍለጊዜ 1 ኮርሱን ለመጨረስ መመዝገብ አለባቸው። ባዮሎጂ B እና NSL B ለሚወስዱ FTNG ተማሪዎች ክፍለጊዜ 1 ምዝገባን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ [MCPS Summer School]() ድረ ገጽ ላይ ይገኛል።

**Q: አንድ ተማሪ በሠመር ትምህርት ክፍለጊዜ 1 ሴሚስተር B ላይ ከሚሰጡ ኮርሶች ባዮሎጂ ወይም NSL እና EOC እንደገና ለመውሰድ መመዝገብ ካልቻለ(ች) ምን ሌሎች አማራጮች ይኖራሉ?**

A: ተማሪዎች ከትምህርት ቀን ውጭ በሚሰጡ ኦንላይን የመመረቂያ ማሟያ (OPTG) ኮርሶችን መመዝገብ፣ በመደበኛ የትምህርት ቀናቸው ኮርሱን መልሰው ለመውሰድ፣ ወይም ሰመር 2025 የሠመር ትምህርት ክፍለጊዜ 1 ላይ ለመመዝገብ መጠበቅ ይችላሉ። የትምህርት ቤት

ካውንስለሮች ስለ እነዚህ አማራጮች ምዝገባን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። መረጃ ለማግኘት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠመር ትምህርት ቤት እና ኦንላይን የምረቃ ድረገጽላይ ይመልከቱ።

**Q: አንድ ተማሪ ባዮሎጂ A ወይም ብሄራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢ ስነመንግስት A ፈተና ካላለፈ(ች)፣ ሴሚስተር B መጨረሻ ላይ EOC ለመውሰድ ይፈቀዳል?**

A: አዎ፣ የፈተናው ውጤት የሚሰላው ሴሚስተር B የመጨረሻ ውጤት ላይ ብቻ ስለሆነ EOC መውሰድ ይቻላል።

## አማራጮች እና ልዩ ሁኔታዎች

**Q: አንድ ተማሪ ከስቴት ውጭ ወይም ፐብሊክ ስኩል ካልሆነ ትምህርት ቤት የኮርስ ክሬዲት ያለው የብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ አስተዳደር ወይም ባዮሎጂ ትምህርት ክሬዲት ይዞ ቢዛወር ምን ይደረጋል? ይህ(ች) ተማሪ EOC ምዘና መውሰድ ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል?**

A: ስለ ዝውውር ክሬዲት አሰጣጥ ያለፈው ልምድ ይቀጥላል። እነዚህን ክሬዲቶች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጭ ያገኘ(ች) ተማሪ የዝውውር ኮርስ እና የፈተና ክሬዲት ይሰጠዋል/ይሰጣታል፤ እና MCAP ስነመንግስት እና/ወይም LS MISA EOC ፈተና መውሰድ አያስፈልገውም/አያስፈልጋትም።

**Q: የላቀ/አድቫንስድ የስነመንግስት (AP) ኮርስ ምደባ ለማግኘት MCAP ስነመንግስት ኮርስ ያስፈልጋል?**

A: የአሜሪካ ስነመንግስት የላቀ ደረጃ ምደባ (AP) ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች የመመረቂያ መስፈርቱን ለማሟላት ኮርሱን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፤ እና ወይም ስነመንግስት EOC ፈተና ወይም AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። EOC ፈተና ውጤት የመጨረሻ የኮርስ ውጤታቸው እንደ 20% አይቆጠርም።

**Q: AP ባዮሎጂ ኦቨ ኢንተርናሽናል ባካሎሬት (IB) ለመመዝገብ ባዮሎጂ ኮርስ LS MISA EOC ፈተና ያስፈልጋል? ከሆነ፣ ባለፈው ዓመት ባዮሎጂ እና MCAP LS MISA የወሰዱ ተማሪዎችስ?**

A: አንድ ተማሪ ከዚህ ቀደም MCPS የባዮሎጂ ኮርስ እና MCAP LS MISA የወሰደ(ች) ከሆነ፣ AP ባዮሎጂ ወይም IB ባዮሎጂ ኮርስ ከወሰደ(ች) EOC እንደገና መውሰድ አያስፈልግም። AP ባዮሎጂን የሚወስዱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች AP ፈተና ወይም EOC ፈተና መውሰድ አለባቸው። የተማሪው(ዋ) የፈተና ውጤቶች በሴሚስተር B መጨረሻ ውጤት ላይ አይሰላም። የስነህይወት ሳይንስ ክሬዲት ለማግኘት AP ወይም IB ባዮሎጂ የሚወስዱ እና ባዮሎጂን ቀደም ብለው ያልወሰዱ ከአስረኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች MCAP LS MISA መውሰድ አለባቸው፤ ነገርግን የፈተና ውጤታቸው በተማሪው(ዋ) ሴሚስተር B የመጨረሻ ውጤት ላይ አይሰላም።

**Q: የኮሌጅ ባዮሎጂ ወይም የስነመንግስት ትምህርት (ጣምራ ምዝገባ) የሚወስዱ ተማሪዎች EOCs መውሰድ አለባቸው?**

A: አዎ፣ ተማሪው(ዋ) ከዚህ ቀደም LS MISA ካልወሰደ(ች)፣EOC መውሰድ ይኖርበ(ባ)ታል። በቅድሚያ የተመደቡ የፈተና ወቅቶች ላይ ፈተናዎችን እንዲወስዱ ለማመቻቸት የት/ቤታቸው

የፈተና አስተባባሪ ያገኛቸዋል። የፈተናው ውጤት በተማሪው(ዋ) የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ላይ አይሰላም። በኮሌጅ ደረጃ የስነመንግስት ኮርስ የክሬዲት መስፈርት የሚያሟላ ምንም አይነት የስነመንግስት ኮርስ የለም፣ስለዚህ ከጣምራ ምዝገባ በፊት MCAP ስነመንግስት EOC መወሰድ አለበት።

**Q: መጪዎቹ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EML) ዘጠነኛ ክፍል በሚገቡበት ዓመት የባዮሎጂ እና/ወይም የብሔራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢ መንግሥት ኮርሶችን መውሰድ አለባቸው?**

A: የኮርሱ ቅደም ተከተል የተስተካከለው በከፍተኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ ላይ ያሉ EMLs የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች EMLs ኮርሶችን በተመለከተ ባለው መመሪያ መሰረት EOC ፈተናዎችን እየወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ስለዚህ፣ አብዛኛዎቹ EMLs እነዚህን ፈተናዎች 10ኛ ክፍል ወይም 11ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ችሎታ የብቃት ደረጃቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲወስዱ ያስፈልጋል።

**Q: አዲስ የመጡ ተማሪዎች EMLs EOC ፈተናዎችን መውሰድ አለባቸው?**

A: ከ12 ወራት በታች ት/ቤት እየተከታተሉ የቆዩ EML ተማሪዎች ተዛማጅ ኮርሶችን ለመውሰድ ከተመዘገቡ EOC ፈተናዎችን መውሰድ አለባቸው። የመመረቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ፈተና መውሰድ አለባቸው። ሆኖም፣ በኮርሳቸው የመጨረሻ ውጤት ላይ EOC አይካተትም።